# ምድብ አምስት (ከ10ኛ — 12ኛ) ክፍል
## 30 ኛ ሳምንት
## የክብር አካል (II)

***የትምህርቱ ዓላማ***

- ❖ ይህ ስለክርስቶስ የክብር አካል የምንማማረው ተከታታይ ትምህርት ክፍል 2 ሲሆን፣
- ❖ በዛሬው ትምህርታችንም ክርስቶስ የክብር አካል በትንሣኤው ይዞ እንደተነሣ እንማራለን፤

***የሚጠና ጥቅስ***

- ❖ *"ደጆቹ ተዘግተው ሳሉ፣ ኢየሱስ መጣ፤ በመካከላቸውም ቆሞ...."* ዮሐ. 20፥19

***መግቢያ***

- ❖ ባለፈው ትምህርታችን ክርስቶስ የተነሣው በክብር እንደሆነ ተምረናል፡፡እኛም ስንነሣ *"ክቡር አካሉን እንዲመስል የተዋረደው ስጋችንን እንደሚለውጥ፡፡"* ፊልጵ 3፥15 አይተናል፡፡
- ❖ ባለፈው ይሄንኑ የሚገልጡት ነጥቦችን የተማርን ሲሆን ዛሬም ይሄንኑ እንቀጥላለን፡-

***ትምህርቱ***

8. ***በተዘጋ በር መግባት እና ከተዘጋ ቦታ መውጣት የተነሣው አካል የክብር አካል እንደሆነ ግልጽ ማረጋገጫዎች ናቸው፡፡***

*"ደጆቹ ተዘግተው ሳለ ......."* ዮሐ. 20፥19 ና 26 በትንሣኤውም ከታተመ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል ወጥቶአል፡፡

ከትንሣኤው በኋላ ነው ሰዎች መቃብሩ ባዶ መሆኑን እንዲያዩ ድንጋዩን ያንከባለለው ከተዘጋ መቃብር ለመውጣቱ ምሳሌ ከሚሆኑን አንዱም ከዚያ በፊትም ከድንግል ማርያም ማኅጸን በሕቱም ድንግልና ተወልዷል፡፡ ይሄን ስንል አንዳንዶች ክርስቶስ እንደተነሳበት ዓይነት ክቡር አካል ይዞ ተወልዷል? ብለው ይጠይቃሉ መልሳችን

9. ***ክርስቶስ የተወለደው የእኛን ዓይነት አካል ይዞ ነው፡፡ ከኃጢአት በስተቀር እኛን መስሎአል፡፡***

የእኛ የሰው ልጆችን በሕርይ ሲወርስ፡- "የሰው ልጅ" ተብሎል በዚህም አድኖናል፡፡ "እንደኛም በሕጻንነት አድጓል" ሉቃ.1፥80፡፡ "ተርቧል" /ማቴ.4፥2/፡፡ ተጠምቷል /ዮሐ. 19፥28/፡፡ ደክሞት ያውቃል (ዮሐ.4፥6)፡፡ "ተኝቷልም" /ማቴ. 8፥24/

10. ***የሰዎችን ባሕርይ ባይነሣ ሕመም አይስማመውም ነበር፡፡ሥጋ የሚሠማውን ሕመም ይሠማው ነበር***፡፡ በሕመም ተሠቃይቶል፡፡ ማለትም የመመታት፣ የመቸንከር ስቃይን ተቀብሏል፡፡ይህም በመስቀል ሳለ በተደጋጋሚ ሆኖል፡፡የቀሬናው ሰው ስምኦን መስቀሉን በመሸከም ያገዘውም ለዚህ ነበር፡፡ የተዋሃደው ሥጋ ባሕርይ መዋቲ /ሟች/ ነበርና ስለ እኛ ሞቷል አድኖናልም፣ የክብር አካል ግን አይታመምም አይሞትምም፡፡

ከዚህም ጌታችን ሲወለድ በታማሚ፣ሟች፣ የሚሠቃይ የሰውን ባሕርይ ይዞ ተወልዷል በዚህ መንገድም ይህ የሰው ባሕርይን ለብሶ ማዳንን ፈጽሞልና፣ ከዚያም በክብር ተነሥቷል

11. ***ዓለምን ከማዳኑ በፊት የነበረው የባሕርይ ክብሩ ኃጢአት የማይስማማው ነበር፡፡***

ሲወለድ፣ በተጸነሰም ጊዜ፣ በምድር ሲመላለስም በመንፈሳዊ ክብር የፈጸማቸው ነገሮች የተከናወኑት በመልካም ፈቃዱ ሲሆን ስጋው ግን ከኃጢአት በቀር እንደእኛ ነበር፡፡ ራሱንም ባዶ አድርጎ የአገልጋዩን ባሕርይ ይዞ ተገኝ፡፡

12. ***ከመለኮት ጋር የነበረው ተዋህዶም የክብሩ አንዱ መሣሪያ ነበር፡፡***

ይህ ተዋህዶ ሰውኛ ባሕርይውን አላስቀረውም፡፡የሥጋን ድካም መራብ፣መጠማት፣ድካም እና ሞትም አላስወገደውም፡፡ይህ ቢሆን መዳን አይፈጽምም ዋጋውንም ያጣ ነበር፡፡ሕማሙ የእውነት ስለነበረም ነው ማዳኑ እውነት የሆነው፡፡ራሱን ባዶ ስላደረገም በትንሣኤው ክብር ሰጠን፡፡ ከመሞቱ በፊት ራሱን ባዶ ስላደረገ *"አባት ሆይ ልጅህን አክብረው ልጅህ እንዲያከብረህ፡፡"*

*"አሁንም አባት ሆይ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በነበረው ክብር አክብረኝ"* ዮሐ.17፥1,5 ብሏል፡፡ይህም ስለ ትንሣኤው የተነገረው ነው፡፡

13. ***ደቀመዛሙርቱ ይህን ክብር አይተው መቋቋም አልቻሉም፡፡***

ወንጌላዊው ዮሐንስ በራዕዩ የእግዚአብሔርን ክብር አይቶ *"እንደሞተ ሰው ሆነ"* ለምን? *"ምክንያቱም ፊቱ እንደ ፀሐይ የበራ አይኖቹም የሚንበለበል እሳት ይመስሉ ነበርና"* ነው፡፡

14. ***ለዚህም ነው ጌታችን ለደቀመዛሙርቱ ሲገለጥ በተለያየ ደረጃና ቀስ በቀስ የትንሣኤውን ክብር ያሳያቸው***

- ለመግደላዊት ማርያም መጀመሪያ ሲገለጥ እትክልት ጠባቂ ሆኖ ነበር፡፡በመጨረሻም ራሱን ገለጠላት፡፡/ዮሐ.20÷14,16/
- ለኤማሁስ መንገደኞች ሲገለጥም ተመሳሳይ ነገር ነው የሆነው፤አብሮቸው እየሄደ አላወቁትም /ሉቃ.24፥16/
- ለደቀመዛሙርቱም ተመሳሳይ እድገት ባለው አገላለጥ ነው የታያቸው ይህ ባይሆን ከትንሣኤው በኋላ ያለውን የክብር አካል ማየት ባልቻሉ ነበር፡፡

15. ***ይህ ማለት በክበሩ ማየት አንችልም ማለት ነው? ካየነውስ እንዴት እና መቼ?***

- የእኛ ሰውኛ ባሕርይ ከሞት ስንነሣ ይለወጣል፡፡የክብር አካሉን እንዲሆንም ሥጋችን ይቀየራል፡፡/ፊልጵ.3÷21/እኛም እናየዋለን ለዚህም ነው ሐዋርያው *"አሁን በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን፣ያኔም ፊት ለፊት እያየዋለን፡፡"* (1ኛ ቆሮ.13፥12)
- *"ፊት ለፊት"* የሚለው ቃል ትርጉም ምንድነው? እንዴትስ ይፈጸማል? ወገኖቼ ለዚህ ዝምታን እመርጣለሁ በሙታን ግን ይሄን እናያለን፡፡

***ማጠቃለያ***

ከዚህ ትምህርት፡-

1. ጌታችን እንደ እኛ ሕማምና ሞት የሚስማማው ሆኖ ተገልጾል፡፡መለኮቱ ከሥጋው ለቅፅበት እንኳን አትለይም፡፡
2. ሰውኛ ባሕሪዩና ከኃጢአት በቀር እኛን መስሎልና መዳንን ፈጽሞአል፣ ከዚያም በትንሣኤው ከብሮአል፡፡

## ይቆየን፡፡